አዋጅ ቁጥር 135/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ

አዋጅ ቁጥር 135/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግሥት ኃፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሃብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፣

የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ግዥ እንዲሁም የግንባታ ሥራ ከመንግሥት ጠቅላላ ሃብት ከፍተኛውን የወጪ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ፤

የመንግሥት ግዥ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ከማድረግ በተጨማሪ ሂደቱ ፍትሃዊ ግልጽ እና አድልዎ የሌለበት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፤

የመንግሥት ግዥ በክልሉ ለሚከናወኑ የኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች መስፋፋት አጋዥ መሣሪያ መሆን ስላለበት፤

በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ **49** ንዑስ አንቀጽ **3 /1/** ድንጋጌ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ የግዥ ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር **135/1998** ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦
1. "ዕቃ" ማለት በጠጣር በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ ምርት መሣሪያ ሸቀጥ እና ኤሌክትሪክ እንዲሁም ከሚገዛው ዕቃ ጋራ ግንኙነት ያለው እና ዕቃዎች ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ ፣ የትራንስፖርት የጥገና ሌላ ተመሳሳይነት ያላቸውን አገልግሎቶች ይጨምራል።
2. "የአገልግሎት ግዥ" ማለት ከዕቃ ፣ ከግንባታ ፣ ሥራና ከምክር አገልግሎት ውጭ ያለማናቸውም ግዥ ነው።
3. "የግንባታ ዘርፍ" ማለት ከህንፃ ፣ ከመንገድ ወይም ከሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች ጋራ በተየያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ ፣ የመልሶ ግንባታ ፣ የማፍረስ ፣ የጥገና ፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን ፣ የመገንባት በባለቤትነት የመያዝ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል።
4. "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸው ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚከናወኑት የጥናት ፣ የዲዛይን ፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት ፣ ለደንበኞች ምክርም ሆነ ሥልጠና የመስጠት ተግባር ሆኖ በባህሪው አዕምሮ አገልግሎት ነው።
5. "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን በግዥ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሣሣይ ውል መሠረት ማግኘት ነው።
6. "ግዥ ፈፃሚ አካል" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤቶች የትምህርተ ተቋም ወይም ተመሣሣይ አቋም ያለው ሌላ ማናቸውም አካል ነው።
7. "የመንግሥት ገንዘብ" ማለት ከክልሉ መንግሥት ግምጃ ቤት ወይም የክልሉ መንግሥት ከፌደራል መንግሥት ካገኘው ድጎማ ወይም የውጪ ርዳታና ብድር ለግዥ ፈፃሚ አካላት የተመደበ ገንዘብ ወይም የግዥ ፍፃሜ አካላት የውስጥ ገቢ ነው።
8. "የመንግሥት ግዥ" ማለት በግዥ ፈፃሚ አካላት በመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው።
9. "አቅራቢ" ማለት ለግዥ ፈፃሚ አካላት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው።
10. "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ነው።
11. "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሃሳብ ያቀረበ ሰው ነው።
12. "የጨረታ ሠነድ" ማለት ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በግዥ ፈፃሚ አካላት ተዘጋጅቶ የሚሰጥ ሰነድ ነው።
13. "የግዥ መመሪያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጣ መመሪያ ነው።
14. "ቢሮ እና የቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው።
15. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. የተፈፃሚነት ወሰን
1. ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኙና ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት በሚተዳደሩ መ/ቤቶች ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** የተደነገገው ቢኖርም ቢሮው አግባብ ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በደህንነት ጉዳዮች ምክንያት ግዥ በተለየ ዘዴ እንዲፈፀም ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቢሮው ግዥዎች በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችል የግዥ ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።

4. ዓለም ዓቀፍ ግዴታዎች
1. ይህ አዋጅ የክልሉ መንግሥት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግሥታት ወይም ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** የተመለከተው ስምምነት ለኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ ግዥ የሚፈጽመው አካል ተፈፃሚ የሚሆነው ልዩ አስተያየት በጨረታ ሠነድ ውስጥ በግልጽ እንዲመለከት ማድረግ ይኖርበታል።

5. ግዥን አማክሎ ስለመፈፀም

ከአንድ በላይ የሆኑ ግዥ ፈፃሚ አካላት አንድ ዓይነት ወይም አገልግሎት ለመግዛት ወይም የግንባታ ሥራ ለማሠራት የሚፈልጉ በሚሆንበት ጊዜ ቢሮው አንድ የመንግሥት መ/ቤት ግዥ በሚፈጽሙት አካላት ስም ግዥውን በቅንጅት እንዲያከናውን ወይም ግዥውን በተጠቃለለ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል የውል ማዕቀፍ እንዲፈርም ሊፈቅድ ይችላል።

6. የሕግ ሠነዶች ሕዝብ እንዲያውቅ ስለማድረግ

ይህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጡ የግዥ መመሪያዎች ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረግ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ በሥርዓት መያዝ አለባቸው።

7. ኃላፊነትና ተጠያቂነት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ስለውሉ አፈፃፀም ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ፣ በተለይም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል፦

ሀ. በተገቢው የሰው ኃይል የተደራጀ የግዥ የሥራ ክፍልና የጨረታ ኮሚቴ የማቋቋም፤

ለ. የጨረታ ኮሚቴ አባላትን የመሰየም

ሐ. የጨረታ ማስታወቂያወችን የማውጣትና አሸናፊዎችን የማሣወቅ፤

መ. የጨረታ አሸናፊውን ከማስታወቅና ውል ከመፈረሙ በፊት በቂ በጀት መኖሩን የማረጋገጥ፤

ሠ. የግዥ ውሎችን የመፈረም፤

ረ. በተጫራቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሣኔ የመስጠት፤

ሰ. የአቤቱታዎችን ቅጅ ፣ የምርመራ ግኝቶችን እና በግኝቶች መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ የያዘ ሪፖርት ለቢሮው የማቅረብ፤

ሸ. ከአሸናፊው ጋር የተደረገው ውል፣ አሸናፊ በሆነባቸው ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፤

ቀ. እንደአስፈላጊነቱ የግዥ ሥርዓትን የሚያስፈፅሙ ሦስተኛ ወገኖችን የመቅጠርና የማስተዳደር።

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት እና ለግዥ ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የመንግሥት ግዥን ለማስተዳደር የተሾሙ ኃላፊዎች በዚህ አዋጅ እና ቢሮው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ።

ምዕራፍ ሁለት
መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች
~~1662~~

8. የግዥ ሰነዶች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከመንግሥት ግዥ ጋር የተየያዙ መዝገቦችንና ሰነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ለ**10** ዓመት ያህል ማቆየት አለባቸው። በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦

ሀ. የሚገዙት ዕቃዎች ፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ፣

ለ. የጨረታ ማስታወቂያ፤

ሐ. የጨረታ ማወዳደሪያ ሐሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ የሰጡ አቅራቢዎች ወይም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፤

መ. ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ ፣ የጨረታ ግምገማ ፣ የውድድሩን አፈፃፀም ፤ ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ. በቀረበው አቤቱታ መሠረት ጨረታውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ውሳኔ የተሰጠበትን አካሄድ የሚያሳይ መረጃ፤

ረ. አግባብ ያለው ሆኖ ሲገኝ ከግልጽ ጨረታ ውጭ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት።

2. የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት። ይሁን እንጂ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልታዘዘ እና በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፦

ሀ. የተጠየቀው መረጃ ይፋ ቢሆን በሕግ የማይፈቀድ ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጐዳ መሆኑ የተገመተ እንደሆነ፤

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **/1/** /መ/ ሥር በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካልሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ ከመመርመር እና

ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፤ እና ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የመወዳደሪያ ሃሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፀው መረጃዎች።

9. አድልዎ ስላለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ **10** የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ ተሳታፊ እንዳይሆን ሊደረግ አይችልም።

10. ልዩ አስተያየት

1. በጨረታ ግምገማ ወቅት፦

ሀ. በኢትዮጵያ የተመረቱ ዕቃወች እስከ **15%**

ለ. በኢትዮጵያ ኩባንያዎች የሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እስከ **7.5%** ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ **20%** በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል።

3. በግዥ አፈፃፀም ረገድ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማትን ለማበረታታት የሚያስችል ልዩ አስተያየት ይደረጋል። ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

11. የግንኙነት ስልት

1. በመንግሥት መ/ቤቶችና በዕጩ ተወደዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሑፍ መደረግ አለባቸው። በጽሑፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በማከታተል በጽሑፍ መረጋገጥ አለባቸው።

2. ቢሮው የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከጽሁፍ በተጨማሪ ወይም በጽሑፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነት እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

12. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

1. በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥው ልዩ ባሕርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፦

ሀ. በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት የፋይናንስ አቅም፤ መሣሪያ እና ሌሎች የመገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ዝግጁነት፤

ለ. ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ፤

ሐ. በዕዳ ያልተያዙ ፤ ያልከሠሩ ወይም የሥራ እንቀስቃሴን ያላቋረጡ ከንግድ ሥራ ያልታገዱ፤ ወይም በእነዚሁ ምክንያቶች ተከሰ ወይም በክርክር ውስጥ ገብቶ አለመገኘት፤

መ. በክልሉ የግብር ሕግ በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታን የተወጡ ሆኖ መገኘት፤

ሠ. በግብር ከፋይነት ተመዝግቦ መገኘትና የተመዘገበና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር።

2. ግዥ ፈፃሚው አካል ዕጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድና ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ለመጠየቅ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሃሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን ፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።

4. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** እና **2** ድንጋጌዎች መሠረት የሚቀርቡትን ሰነዶች እና የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብቃት መገምገም አለበት።

5. ግዥ ፈፃሚው አካል ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሐሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ በአመዛኙ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠባቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጭ እንዲሆኑ ለመወሰን ይችላል።

13. የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር

1. ስለግዥው ምንነት ፤ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር ወይም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባሕርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው።

2. የቴክኒክ መግለጫው ግዥ ፈፃሚው አካል ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት ጠቀሜታ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን፣ መለኪያውን መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊውን የሚያሟላ መሆኑ የሚያረጋግጥበትን ሥርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት።

3. በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጀው የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫ አግባብነት እስካለው ድረስ፦

ሀ. በዲዛይን ወይም ባሕሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣

ለ. አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

4. የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጐት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ሰም፣ ፓተንት ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም።

14. ጨረታውን የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ስለማድረግ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ጨረታን የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ።

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ **1** በተመለከተው መሠረት ግዥ ፈፃሚ አካላት ጨረታን የመወዳደሪያ ሃሳብና የዋጋ ማቅረቢያን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደረጉበትን ምክንያት በተጠየቁ ጊዜ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መግለጽ አለባቸው።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** ድንጋጌ ቢኖርም ግዥ ፈፃሚ አካላት የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም።

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ **1** በተመለከተው መሠረት ጨረታን ፣ የመወዳደሪያ ሃሳብንና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም።

15. በዕጩ ተወዳዳሪዎች ስለሚሰጥ መደለያ

ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ግዥ የሚፈጽመውን አካል ወይም ሌላ የመንግሥት መ/ቤት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ የሰጠ ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል የገባ ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት በመስጠቱ በተጨባጭ የተደረሰበት እንደሆነ ግዥውን የሚፈጽመው አካል የዕጩ ተወዳዳሪውን ጨረታ የመወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ውድቅ ማድረግ አለበት።

ምዕራፍ ሦስት
የግዥ ዘዴዎችን ስለመምረጥ

16. የግዥ ዘዴዎች

1. በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው።

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ **17-21** በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል።

3. በቂ የኢኮኖሚ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ ቢሮው ከአንቀጽ **17-21** ባልተጠቀሱት ሌሎች ምክንያቶች ከግልጽ ጨረታ ውጪ ግዥ በሌሎች ዘዴዎች እንዲፈፀም በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል።

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት በምክንያት የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው።

17. በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ይሆናል፦

ሀ. ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ በባሕርይው በከፍተኛ ደረጃ ውስብስብ ወይም የተለየ በመሆኑ ምክንያት ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚሆን ሲሆን ወይም

ለ. በርካታ የጨረታ ሰነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ዕቃው ፣ የግንባታ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከሚያወጣው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን ሆኖ ሲገኝ።

18. ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ **37** በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ የሚፈጽሙት በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ መሆን የለበትም። ሆኖም ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ግዥ ፈፃሚ አካላት ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፦

ሀ. ዕቃው የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ የተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፤

ለ. በልማት ደረጃቸው በአንጻራዊነት ወደ ኋላ የቀሩ ወረዳዎች በቂ አቅራቢዎች የማይገኙና በአቅራቢያቸው የተሻለ ከተማ አለመኖሩ በቢሮው ሲረጋገጥ፤

ሐ. ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈልግ፣ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈፀም የሚገዛው መሣሪያ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚው አካል ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም ከአገልግሎቱ ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያ አቅራቢ ተጨማሪ አቅርቦቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

መ. በማስፈፃሚያ መመሪያው የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ አስቀድመው ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና በቴክኒካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ. በማስፈፃሚያ መመሪያው የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ አሸናፊው በግልጽ ወይም በውስን ጨረታ ዘዴ ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ፕሮጀክት የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች በድጋሚ እንዲሠሩ ማድረግ በማስፈለጉ አዲስ የግንባታ ሥራ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፣ ~~1666~~

ረ. በማስፈፃሚያ መመሪያው የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያው የምክር አገልግሎት ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ በመጠናቀቁ ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሰ. በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ ሲያጋጥም፤

ሸ. ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለግዥ ፈፃሚው አካል ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የዕቃ ግዥ ሲሆን።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** ድንጋጌ በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሠማሩ ድርጅቶች ለሚሸጧቸው ዕቃዎች ግዥ የሚያገለግል ሲሆን በመደበኛ አቅራቢነት ከተሠማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፀሙ ግዥዎችን አይጨምርም።

3. ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ በመጠቀም መግዛት ይችላሉ።

19. በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታ

ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ **38** በተደነገገው መሠረት በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከአንድ ግዥ ውል ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ድርሻ **50%**ና ከዚያ በላይ ሲሆን ነው።

20. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ **39** በተደነገገው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ግዥው በቢሮው በሚወጣው የማስፈፀሚያ መመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው።

21. በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ **40** በተመለከተው መሠረት በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ ግዥን መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

1. ለሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመ/ቤቱ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና መ/ቤቱ የግዥ ፍላጐቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሔ ለማግኘት፦
   ሀ. ጨረታን ፣ የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦት መወዳደሪያ ሃሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን በሥራ ላይ ማዋል ሲፈለግ፣
   ለ. በሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ ምክንያት ከአቅራቢዎች ወይም ሥራ ተቋራጮች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ።
2. መጠናቸው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን የሚጨምር ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፣
3. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጐ ተጫራቾች ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና መ/ቤቱ ሌላ ጨረታ ቢወጣ ውጤት መገኘቱ አጠራጣሪ ነው ብሎ ሲያምን።

22. የኮንትራት ግዥ አፈፃፀም

የእቃና አገልግሎት ግዥን በሚመለከት የኮንትራት ግዥ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ቢሮው ሊያወጣ ይችላል።

ምዕራፍ አራት

ግልፅ ጨረታ

23. የጨረታ ማስታወቂያ

1. የጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ በአንድ ጋዜጣ ላይ መውጣትና ከተቻለ ደግሞ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ጭምር መገለጽ አለበት።
2. ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ ይህንን አዋጅ ለመፈፀም በሚወጣው መመሪያ ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም።
3. መገናኛ በሌለባቸው አካባቢዎች የአካባቢ ግዥን ለማበረታታት ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

24. የጨረታ ጥሪ

የጨረታ ጥሪ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

1. የግዥ ፈፃሚውን አካል ሙሉ ስምና አድራሻ፤
2. ዕቃው መቅረብ ወይም ሥራው መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ጨምሮ የዕቃውን፤ የግንባታ ሥራውን እና የአገልግሎቱን አጭር መግለጫ፤
3. የጨረታውን ሰነድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እና የጨረታ ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣
4. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበትን ቦታ እና የማቅረቢያውን የመጨረሻ ጊዜ፤
5. ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሲከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን በራሳቸው ፈቃድ ባይገኙ ግን ጨረታውን ከመክፈት የማይታገድ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፤
6. መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ።

25. የጨረታ ሰነድ

በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ ፤ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሰነድ በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት። በተለይም ሰነዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፦

ሀ. የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፤

ለ. የጨረታ ሰነዱን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የጨረታ ሰነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ የጨረታውን ሰነድ የሚከፈትበትን ቀን፤ ሰዓት እና ቦታ፤ እንዲሁም ተጫራቹ ወይም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ፤

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረቢያ ቅፆች እንዲሁም አግባብነት እስካላቸው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅጾች፤

መ. ከዋናው የጨረታ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸው ተጨማሪ ኮፒዎች፤

ሠ. የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች፣

ረ. እንደአግባብነቱ ዕቃውን ለማቅረብ ወይም ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተውን ጊዜ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር፤

1668

ሰ. ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙንና ሕጋዊ እና ወቅታዊ የንግድ ፈቃድ እንዲሁም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለትን መረጃ፤

ሸ. ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

ቀ. ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፤

በ. ግዥውን የሚፈጽመው አካል የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን።

26. የጨረታ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል

የጨረታ ሠነዶች ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት እና ሠነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ ዋጋ በተፋጠነ ሁኔታ እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርሱ መደረግ አለበት።

27. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

የጨረታ ሰነዶችን የሚለውጥ ማናቸውም ማሻሻያ በተሻሻለው ተጨማሪ የጨረታ ሰነድነት ሰነዶችን ለገዙ ሁሉ መላክ አለበት።

28. በጨረታ ማስከበሪያ

1. በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተወሰነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር በተቀማጭ ገንዘብ ወይም በጨረታ ዋስትና መልክ የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል። የጨረታ ማስከበሪው መጠን ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ በጨረታው የማይሳተፉበትን ለማስቀረት የሚያስችል ሆኖ ፤ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ከተወሰነው መጠን ያላነሰ መሆን አለበት።

2. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው አይመለስለትም።

29. የጨረታ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል

1. የጨረታ ሰነድ በጽሑፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኤንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለፀው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት። ግዥ ፈፃሚው አካል በተጠየቀ ጊዜ የጨረታ ሰነዱ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳይ ደረሰኝ ለተጫራቹ መስጠት አለበት።

2. ለጨረታ ማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ሳይከፈት ለተጫራቹ መመለስ አለበት።

30. ጨረታን ስለመክፈት

1. ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው ለጨረታ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የጨረታ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የተረከባቸውን የጨረታ ሰነዶች መክፈት አለበት።

2. ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጨረታ ሰነዱ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ መጋበዝ አለባቸው።

3. የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ ባለ ድምጽ መነበብ እና መመዘገብ ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ የጨረታ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ ድምር ከፍ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን አለበት።

31. የጨረታ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

1. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ግዥ ፈፃሚው አካል ተጫራቾች ባቀረቡት የጨረታ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ በጨረታው ሰነድ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሃሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል። ግዥ ፈፃሚው አካል እነዚህን ማስተካከያዎች የጨረታ ሰነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ መግለጽ አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው።

4. በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባሕሪያት ፤ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል። ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሃዝ ተገልጾ በጨረታ ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት።

5. ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ለውድድር እንዲቀርቡ መፍቀድ የለበትም፦

ሀ. ተጫራቹ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 25 /ሰ/ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ. የቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ተፈላጊውን የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ።

6. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው ሥርዓት እና የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊው ሁኔታዎችን ያሟሉ የጨረታ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት። በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

7. በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው፦

ሀ. በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠለትና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ወይም

ለ. ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታው ሰነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበትን መስፈርት የገለፀ ከሆነ በጨረታ ሰነዱ የሰፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወሰነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ የቴክኒክ፣ የዋጋና የማቅረቢያ ጊዜ ጥምር ግምገማ የተሻለ ደረጃ ያገኘ ሲሆን ነው። ሆኖም በፊደል ተራ ቁጥር ለ የተጠቀሰው መስፈርት በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተና በአጎዝ ሊቀየር የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለጽ መሆን አለበት።

8. ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነድ ምርመራና ግምገማውን ውጤት በአጭሩ የሚገልጽ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።

32. በሚስጢር ስለሚያዙ አሠራሮች

1. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ ከማብራሪያ፣ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በምስጢርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፤ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለጽበት ጊዜ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለባቸውም።

2. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ማንኛውም ተጫራች በማናቸውም አኳኋን የጨረታውን ምርመራና ግምገማ ለማዛባት መሞከር የለበትም።
3. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ማናቸውም ዕጩ ተወዳዳሪ ከጨረታው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከግዥ ፈፃሚው አካል ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችለው በጽሑፍ ብቻ ይሆናል።

33. በጨረታው አሸናፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ተጫራቾች ያቀረቡትን የመወዳደሪያ ሃሳብ አሻሽለው እንዲያቀርቡ በቅድመ-ሁኔታነት መጠየቅ የማይቻል ስለመሆኑ

ማናቸውም ተጫራች በጨረታው ሰነድ ከተመለከተው ውጭ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም በሌላ አኳኋን ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንኑ ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ በቅድመ-ሁኔታነት ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም።

34. አሸናፊነትን ስለመግለጽና ውል ስለመፈራረም

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የመወዳደሪያ ሃሳቡ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለጽ አለባቸው። ለተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታውን አሸናፊ ተጫራች የአሸናፊነት ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል።
2. በግዥ ፈፃሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመሥርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሰነድ ሲፈረም ይሆናል።
3. ግዥ ፈፃሚው አካል ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸውን የሚገልፀው ማስታወቂያ ከመድረሱ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ **43** የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለበትም።

35. የውል ማስከበሪያ

አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት በግዥ ፈፃማው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚው አካል መስጠት አለበት። የውል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያው ዓይነት መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

ምዕራፍ አምስት
ስለሌሎች የግዥ ዘይዎች

36. ውስን ጨረታ

የውስን ጨረታ ሥርዓቶች ከግልጽ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ ውስን ጨረታ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ልዩ አሠራሮች የሚከተል ይሆናል፦

1. የጨረታ ጥሪው በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጐት ላላቸው በተወሰኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቻ ይላካል። ተጫራቾች አድልዎበሌለበት ሁኔታ መመረጥ ያለባቸው ሲሆን የሚቻል እስከሆነ ድረስ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ የሆነ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆን አለበት፤
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ የሚደረግላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመርጡት ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውንና የሚፈለገውን ግብር የከፈሉ ሆነው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቸው መካከል ይሆናል። አመራረጡ ለነዚህ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊ የሆነ እድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል።
3. ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ጥሪ ቢደረግላቸው በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ መሆኑን መግለጽ እንዲችሉ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ **23** ንዑስ አንቀጽ **1** በተደነገገው መሠረት ማስታወቂያ ለማውጣት ይችላል።
4. ግዥ ፈፃሚው አካል የግዥውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚስፈልግ መሆን ያለመሆኑን ይወስናል።

37. ከአንድ አቅራቢ ሰለሚፈፀም ግዥ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ **18/1/** በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም ሲፈልግ ግዥውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት ፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ከአቅራቢው ጋር በግልጽ መደራደር አለባቸው። ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ በአንቀጽ **18/1/** መሠረት ግዥ ለመፈፀም የሚደረሰው ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል መረጋገጥ አለበት።
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ **18/2/** በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፀም ግዥ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይደለም።

38. በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ መሠረት ስለሚፈፀም ግዥ

1. የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ከሦስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ በግዥ ፈፃሚው አካል ለሚመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል። የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀው ወጪ በመመሪያው ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉት ሁሉ ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ከተጠየቁ በኋላ ይሆናል።
2. የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦
   ሀ. የግዥ ፈፃሚውን አካል ሙሉ ስምና አድራሻ፣
   ለ. የሚፈለገውን አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ጽሑፍ፣
   ሐ. የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፣

   መ. የመወዳደሪያ ሃሳቦችን፣ መገምገሚያ መስፈርቶችን፣ ለዋጋና ለሌሎች መሥፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፣ መስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሃሳብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን፣
   ሠ. የመወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበትን ቦታ@ጨረሻ ቀን።
3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሃሳብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።
4. ግዥ ፈፃሚው አካል አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሃሳቡ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ባሕሪ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማካሄድ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ መፍቀድ ይችላል።
5. ግዥውን የሚፈጽመው መ/ቤት በሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂየ ሰነድ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት እና ሥርዓት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ተወዳዳሪ ነው።

39. በዋጋ ማቅረቢያ ስለሚካሄድ ግዥ ሥርዓት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የዋጋ ማቅረቢያን ብዛት ካላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች መጠየቅ አለባቸው። ስለሆነም የሚቻል እስከሆነ ድረስ ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይገባል።
2. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛትና የማቅረቢያ ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጐቶች የሚይዝ መሆን አለበት።
3. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያውን ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።
4. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ለሚያሟላ እና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀረበው ዋጋ ባነሰ ሁኔታ የሚፈለገውን ዕቃ ማግኘት የሚቻል ከሆነ የመ/ቤቱ ኃላፊ በቀጥታ እንዲገዛ ሊወሰን ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ /ፕሮፎርማ/ ዋጋ ሞልቶ የተወዳደረ አቅራቢ ለዚሁ ዕቃ ዋጋ ቀንሶ በመሸጥ ሊደራደር አይችልም። የመ/ቤቱ ኃላፊ የገበያ ዋጋ የሚያጠናለትን ሠራተኛ ሊወስን ይችላል።
5. የግዥ ትዕዛዙ የደረሰው ተወዳዳሪ በትዕዛዙ መሠረት የሚፈጽም መሆኑን በጽሑፍ ማረጋገጥ አለበት።

40. የሁለተኛ ደረጃ ጨረታ

1. ጨረታው የሚከናወነው በሁለተኛ ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን በጨረታው ሰነድ ተጫራቾች በመጀመያው ደረጃ ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ጥሪ ያደርጋል። በጨረታው ሰነድ አቅራቢዎች ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫዎች፣ ጥራት ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባሕርያት እንዲሁም የአቀርቦቱን ውል ቃሎችና ሁኔታዎች እና አግባብነት እስካለው ድረስ የአቅራቢውን የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልፁ ሊጠየቁ ይችላል።
2. በሁለተኛው ደረጃ ጨረታ ዘዴ በሁለተኛው ደረጃ ላይ ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል የጨረታ ሃሳባቸው ውድቅ ያልተደረገባቸውን ተጫራቾች አንድ የተለየ ዝርዝር በሚመለከት ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል። ይህንን የተለየ ዝርዝር ሲያዘጋጅ መ/ቤቱ በመጀመሪያው የጨረታ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባሕርያት እና ሰነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መሥፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሠረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባሕርያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል። እንደዚህ ያሉት ማናቸውም ሰረዛዎች ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለጽ አለባቸው። የመጨረሻ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ያልፈለገ ማናቸውም አቅራቢ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ሳይደረግበት ከጨረታው ውድድር እራሱን ሊያገል ይችላል።
3. በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ አሸናፊውን ተጫራች ለመወሰን ግመገማ እና ውድድር የሚያደርገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ **25** በተደነገገው መሠረት ይሆናል።
4. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

ምዕራፍ ስድስት
ዓለም ዓቀፍ የግዥ ዘዴ

41. ዓለም ዓቀፍ የግዥ ዘዴ

1. ዓለም ዓቀፍ ግልጽ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የውጭ ኩባንያዎች በጨረታው ተሣታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በግልጽ ጨረታው ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት እና ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው።
2. ዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ በምዕራፍ **4** የተጠቀሱትን እንዲሁም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች መከተል አለበት፦
   ሀ. የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነዶች የዓለም ዓቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው።
   ለ. የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም በቂ ሥርጭት ባለው እና ዓለም ዓቀፍ ውድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ ላይ የጨረታ ማስታወቂያው መታተም አለበት።
   ሐ. የጨረታ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳባቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን አለበት።
   መ. የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር በዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበትን ደረጃ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

ሠ. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸው እንዲሁም የሚያቀርቡበትን ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው እና በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት።

ረ. አጠቃላይ እና ልዩ ልዩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በዓለም ዓቀፍ ንግድ የሚሠራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

42. ሌሎች ዓለም ዓቀፍ ሥርዓቶች

ከግልጽ ጨረታ ውጪ እንዲወሰን ጨረታ ወይም የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቅና ባሉት የግዥ ዘዴዎች የውጭ አገር ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ከታመነበት ከምዕራፍ አራት በተጨማሪ እስከተቻለ ድረስ የአንቀጽ **4** ንዑስ አንቀጽ **2** ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

1674

ምዕራፍ ሰባት

በመንግሥት ግዥ ላይ ለቢሮው ወይም ለግዥ ፈፃሚ አካላት ስለሚቀርብ አቤቱታ

43. ጠቅላላ

1. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ግዥውን በፈፀመው አካል የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር የዚህን አዋጅ፣ የማስፈፀም መመሪያውን ወይም እነዚህን መሠረት በማድረግ የተላለፉ ትዕዛዞችን ይጥሳል ብሎ የሚያምን ዕጩ ተወዳዳሪ በአስተዳደር አካላት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥለት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **1** በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም፦

ሀ. በምዕራፍ **3** በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፤

ለ. በአንቀጽ **14** መሠረት ጨረታን፤ የመወዳደሪያ ሃሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ።

3. ግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ውል ከፈረመ በኋላ ውድድሩን ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአስተዳደር አካላት ሊታዩ አይችሉም።

44. ለግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. በግዥ ፈፃሚው አካል በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ይሆናል። ዕጩ ተወዳዳሪው አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በ **5** /በአምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል።

2. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ የግዥውን አፈፃፀም ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ **15** /በአስራ አምስት/ ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት።

3. የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ **2** በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ የግዥ ፈፃሚው አካል ውሣኔ ከተገለፀበት ቀን አንስቶ የሚቆጠር **5** /አምስት/ የሥራ ቀን ውስጥ ለቢሮው አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

45. ለቢሮው ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. ቢሮው አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ አግባብ ላለው ግዥ ፈፃሚ አካል አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልካል። አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደተላከ ግዥ ፈፃሚው አካል ቢሮው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት።

2. ቢሮው የዕጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረገው በስተቀር፣ ግዥ ፈፃሚው አካል ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሳኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ ወይም ከሕግ ውጭ የሆነውን የግዥ

ስርዓት እንዳይከተል ሊያደርግ ወይም ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ ሊያስተላልፍ፣ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሳኔዎች በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል ሥራውን እንዲያከናውን ወይም ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

3. ቢሮው በአቤቱታው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ለማወቅ ፍላጐት ላላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅና ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች እና ከግዥ ፈፃሚው አካል የቀረበውን መረጃ እና መከራከሪያ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት።

4. ቢሮው አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን መፍትሔ ርምጃዎች በመጥቀስ ውሣኔ መስጠት አለበት።

ምዕራፍ ስምንት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

46. ጥፋቶችና ቅጣቶች

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው፦

ሀ. በሕግ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባ በስተቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወኑ ማናቸውንም ክፍያ ከተቀበለ፣

ለ. የመንግሥት መ/ቤትን የግዥ አሠራር በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣

ሐ. ሕጉን የጣሰ ወይም በሌላ ማንኛውም ሰው ሕጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣

መ. በፈቃደኝነት በማናቸውም መንገድ ሐሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረመ ወይም የመዘገበ ወይም ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት የሰጠ፣

ከብር **25000.00** /ሃያ አምስት ሺህ/ በማያንስና ከብር **35000.00** /ሰላሳ አምስት ሺህ/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ **10** /አሥር/ ዓመት በማያንስና ከ **15** /አሥራ አምስት/ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የተቀጠረ ማናቸውም የግዥ ባለሙያ በዚህ አዋጅ ይፋ እንዲሆን ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፦

ሀ. ግዥውን በማስፈፀም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚህ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ግዥን በማከናወን ረገድ ያለውን ሥልጣን ለማስፈፀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል ግዥውን በሚፈፀመው መ/ቤት ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ሐ. ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር **10000.00** /አሥር ሺህ/ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ **2** /ሁለት/ ዓመት በማያንስ፣ ከ **5** /አምስት/ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል ግዥውን በሚፈጽመው መ/ቤት የተቀጠረ ሠራተኛ፦

ሀ. በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይም ለሥጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ወይም

ለ. በግዥ ተግባር ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግዥ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር **50** ሺህ የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ **10** ዓመት በማያንስ ከ **20** ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

4. ማንኛውም ሰው በመንግሥት ግዥ ላይ ለተሾመ ወይም ለተመደበ ሰው፦

ሀ. የቀረበለትን ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በሥራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ወይም የሚወስደውን እርምጃ ለማዛባት ወይም፤

ሰ. በመንግሥት ግዥ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም ወይም ድርጊቱ ይፈፀም ዘንድ እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈፀም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንዲስማማ፣ እንዲመሳጠር ወይም እንዲፈቀድ ለማድረግ በማሰብ ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት፣ ከቀረበለት ወይም ከሰጠው ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ ከብር **50** ሺህ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ **10** ዓመት የማያንስ እና ከ **20** ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

47. ስለግልግል

በግዢ ፈፃሚውና በአቅራቢው መካከል አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ በቅድሚያ ጉዳዩ የሚታየው ሁለቱ ወገኖች በሚመርጧቸው ገለጋዮች አማካኝነት ይሆናል።

48. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው የዚህን አዋጅ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ እና የአዋጁን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

49. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሂደት ላይ ያሉና ውል የተያዘባቸው ግዥዎች በሥራ ላይ ባለው የክልሉ ግዥ መመሪያ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

50. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

51. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ሰኔ 8 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

11th Year No 20

11th Year

Proclamation No. 135/2006

The Amhara National Regional State public Procurement Procedure Determining Proclamation

A Proclamation Issued to Determine Public Procurement Procedure of the Amhara National Regional State.

WHEREAS, the economic and efficient use of public funds is essential in order that the Regional Government properly discharge its responsibility;

WHEREAS, Procurement of goods, works and services constitute a major share of public expenditure;

WHEREAS, public procurement must be carried out in a manner which is not only economic and efficient but also fair, transparent and non-discriminatory;

WHEREAS, public procurement may also be instrumental to the expansion of economic development activities of the Region;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-article 3/1/ of Article 49 of the Revised constitution of the Amhara National Region, the following is proclaimed.

PART ONE
GENERAL /PROVISIONS/

1. *Short Title*

   This proclamation may be cited as "Public Procurement procedure Determining Proclamation No. 135/2006."

2. *Definitions*

   In this proclamation, unless the context requires otherwise:

   1) ***"Goods" means raw material, product, equipment and commodities in solid, liquid or gaseous form, and electricity as well as installation, transport, maintenance and other similar services related to the supply of goods whose value do not exceed that of the goods themselves.***
   2) ***"Service procurement" means any procurement other than goods, construction works and consultancy services.***
   3) ***"Construction works" means works associated with construction, reconstruction, demolition, repair, renovation of a building, road,. Or infrastructure works as well as services incidental to works, if the value of those services do not exceed that of the works themselves and include contracts of transfer construction, ownership and operating the work.***
   4) ***"Consultancy Services" means a service of intellectual nature provided by consultants using their professional skills through undertaking activities of study, design,***

organizing various projects and offering advice as well as trainings to clients.

5) "Procurement" means obtaining construction works and services though purchasing, renting, or pursuant to any other similar contractual means.

6) "Procuring entity" means public body, which is partly or wholly financed by the Regional Government budget, education institutions or any other body having similar status.

7) "Public Funds" means and monetary resources appropriated to procuring entities or internal revenue of procuring entities from the Regional Government treasury or subsidy which the Federal Government grants to the Regional Government or from foreign aid and loan.

8) "Public procurement" means procurement by procuring entities using public funds.

9) "Supplier" means a physical or juridical person who enters in to contract with a procuring entity to supply goods or services or to undertake construction works.

10) "Candidate" means a physical or juridical person invited to take part in public procurement or seeking to be so invited.

11) "Bidder" means a physical or juridical person submitting a bid.

12) 'Bid Documents" means documents prepared by the procuring entity to bidders as a basis for preparing their bids.

13) "Procurement Directive" means a directive to be issued by the Bureau pursuant to this proclamation.

14) "Bureau and Bureau Head" means Bureau of Finance and Economic Development and Head of same Bureau respectively.

15) "Person" means natural or juridical person.

3. Scope of Application

1) This proclamation shall be applicable on the procurement carried out by offices which are in the Region and fully as well as partially financed by the Regional Government budget.

2) Notwithstanding sub-Article 1 of this Article, the Bureau, in consultation with Heads of the relevant public bodies, may in the interest of security affairs decide to use various procedures, in which case the Bureaus shall issue a directive to implements to be carried out economically and efficiently.

4. *International Obligations*

1) To extent that this proclamation is inconsistent with an obligation of the Regional Government under or arising out of an agreement with one or more other states or with international organizations, the provisions of that agreement shall be applicable thereon.

2) Where an agreement referred to in sub-Article 1 of this Article contains a preference or preferences in favor of national and resident bidders, a procuring entity shall ensure that the applicable preference or preferences are clearly stated in the bidding documents.

5. *Centralizing the execution of procurement*

If more than one procuring entity needs the same kind of goods, works or services, the Bureau may allow one entity of government offices to procure such items in coordination on behalf of other entities or to enter into frame work agreements based on aggregate purchase.

6. *Public accessibility of legal Documents*

This proclamation and procurement directives to be issued by the Bureau pursuant to this proclamation shall be made accessible to the public and systematically maintained for use

7. *Responsibility and accountability.*

1) Procuring entities having overall responsibility for the procurement process, and contract implementation shall have the following duties in particular;

a. Establish a procurement unit staffed at an appropriate level and tender committee;

b. Appoint member of tender committee;

c. Advertise bid invitations and notify winning bidders;

d. Ensure the availability of adequate budget for procurement activity before notifying bid winners and signing a contract;

e. Sign contracts for procurement activities;

f. Investigate complaints by bidders and render decisions thereon;

g. Submit a copy of any complaints, investigation finding and reports of the findings and decisions to the Bureau;

h. Ensure that the implementation of the awarded contract is in accordance with the terms and conditions of the award;

i. Employ and manage third parties who cause the execution of procurement activities as deemed necessary.

1679

2) ***Procuring entities and Persons employed appointed to manage public procurement are responsible and accountable for actions taken pursuant to this proclamation and to directives to be issued by the Bureau.***

CHAPTER TWO
BASIC PROCUREMENT PROVISIONS

8. Procurement Document

1) ***Procuring entities must maintain record and documents regarding their public procurement for a period of ten years from the date of concluding any procurement proceeding which for each proceeding shall include;***
   a. ***A brief description of goods, construction works or services to be procured;***
   b. ***The invitation to bid;***
   c. ***The name and addresses of suppliers that submitted bids proposals or quotations or the name and address of the winning bidders;***
   d. ***The evaluation criteria stipulated and applied and a summary of the evaluation and comparison of bids, proposals and quotations received;***
   e. ***Information of any decision to suspend or cancel proceedings after having been initiated; and***
   f. ***The grounds for using a procurement procedure other than open bidding where found appropriate.***

2) ***The record concerning any proceeding shall on request, and once the proceedings have resulted in a contract or have otherwise been terminated, be made available to candidates who participated in the proceedings, However, expect when order to do so by a competent court and subject to the conditions of such an order, the procuring entity shall not disclose.***
   a. ***Information requested if its disclosure would be contrary to law, would impede law enforcement, would not be in the public interest, would prejudice legitimate commercial interest of the parties or would inhibit fair competition;***
   b. ***Information relation to the examination and evaluation of bids proposals or quotations and the actual content of bids, proposal or quotations other than in the summary form referred to in sub article 1(d).***

9. Impartiality

Without prejudice to Article 10 of this proclamation, candidates shall not be excluded from participation public procurement on the basis of nationality, race or any other criterion not having to do with their qualifications.

10. Preference

1) ***A preference margin of:***
   a. ***Up to 15% for goods produced in Ethiopia: and***

b. Up to 7.5% for construction works carried out by Ethiopian nationals; shall be granted in the evaluation process.

2) For the purpose of sub Article 1 of this Article, any good to which more than 20% or the value added occurs in Ethiopia shall be defined as one which is produced in Ethiopia.

3) There shall be made a preference with a view to encouraging micro and shall trade and industry institutions with regard to procurement execution. Particular shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

11. Form of communications

1) Communications between government offices and candidates shall be in writing. Communications in any other from shall be referred to and confirmed in writing.

2) Subject to necessary safeguards with regard to authenticity and confidentiality, and when technical conditions so permit, the Bureau may determine the extent by the communication by electronic means may be used in addition to or instead of writing.

12. Qualification of candidates

1) In order to participate in public procurement candidates must quality by meeting the following criteria and such other criteria, as the procuring entity considers appropriate under the circumstance;

a. That they have readiness with the necessary professional and technical qualifications and competence, financial resources, equipment and other physical facilities, managerial capability experience in the procurement object, reputation, and the personnel to perform the contract;

b. That they have the legal capacity to enter into the contract;

c. That they are not insolvent, in receivership, bankrupt or being wound up, their business activities have not been suspended, or they are not subject to legal proceedings or they do not enter in to disputes due to a s such grounds;

d. That they have fulfill their obligations to pay taxes according to the Regional state tax laws; and

